# የCSA አስገዳጅ ያልሆነ ስምምነት

ይህ የCSA አስገዳጅ ያልሆነ ስምምነት (ከዚህ በኋላ በዚህ ውስጥ "ስምምነቱ" እየተባለ የሚጠቀሰው) ዛሬ ________ (ቀን) አርሊንግተን፣ ቨርጂንያ ውስጥ በአንድ በኩል በ ________________________________ (እድሜው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ልጅ) የትውልድ ቀን __________ ወላጅ/ጆች/ሕጋዊ አሳዳጊ/ዎች እና በሌላ በኩል በ ________________________________ በአርሊንግተን፣ ቨርጂንያ የማህበረሰብ ፖሊሲ እና አስተዳደር ቡድን በተሾመው እና የዚሁ ወኪል ሆኖ በሚሰራው የመንግስት ኤጀንሲ ________________________________ (ከዚህ በኋላ በዚህ ውስጥ "ኤጀንሲው" እየተባለ በሚጠቀሰው) መካከል ተፈረመ።

☐ የህጻኑ በግዛት በተፈቀደ የህጻናት ማሳደጊያ ወይም ፍቃድ የተሰጠው አገልግሎት መስጫ ውስጥ ምደባ በሚከተሉት ምክንያቶች ከተደረገ በዚህ ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ፥

- የህጻኑን ጥቅሞች ለማስከበር፤
- በአሁኑ ወቅት የህጻኑን ፍላጎቶች ለማሟላት እጅግ ተገቢና በዝቅተኛ ደረጃ ገዳቢ መቼት ስለሆነ፤ እና
- በህጻኑ የቤተሰብ ጥናት እና የእቅድ ዝግጅት ቡድን (FAPT) አባላት እና ወላጆች ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎች ስምምነት ስለተደረገበት።

☐ ምደባው በፍርድ ቤት የታዘዘ ከሆነ እና በወላጅ ፍቃደኝነት ያልተደረገ ምደባ ከሆነ በዚህ ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ።

**የምደባ ስልጣን**

እኔ/እኛ ከላይ የተጠቀሰው ለአቅመ አዳም ላደረሰው ሕጻን ልጅ ወላጅ/ጆች/ሕጋዊ አሳዳጊ/ዎች እንደመሆኔ/ናችን መጠን ለህጻኑ የሚበጀውን የማቀድ ህጋዊ ስልጣን ያለን ሲሆን ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በግዛቱ ተቀባይነት ያገኘ ማሳደጊያ ቤት ወይም ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ውስጥ በ _________ (ቀን) በፈቃዳችን እንዲገባ አድርገናል።

**መብቶችና ኃላፊነቶች:**
**ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች)**

1. የህጻን ልጄ/ጃችን ህጋዊ ጠባቂ ነኝ/ነን።
2. ግቡ አስፈላጊነቱ እንደታመነበት ወዲያውኑ ልጄ/ጃችን ወደ ቤተሰብ እንዲመለስ ማድረግ እንደሆነ እስማማለሁ/እንስማማለን።
3. ባለኝ/ን አቅም/ችሎታ ሁሉ የሚከተሉትን አደርጋለሁ/እናደርጋለን፥
   - ይህ ስምምነት ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ውስጥ በሙሉ በአገልግሎቶቹ ጥናት፣ እቅድ ዝግጅት እና ትግበራ ሁሉም ጉዳዮች ላይ በንቃትና ወጥነት ባለው መልኩ እሳተፋለሁ፣
   - ከልጄ/ጃችን እና የቤተሰባችን ፍላጎቶች ጋር በተያያዘ በሚደረጉ የFAPT የአገልግሎት እቅድ ዝግጅት፣ ክለሳና ቁጥጥር ስብሰባዎች ላይ በመታደም እና እሳተፋለሁ፣
   - በቤተሰብ ህክምና ክፍለ ጊዜዎች፣ የወላጅ ስልጠና እና/ወይም በግል የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ (IFSP) ስር በሚገለጸው መሰረት ለቤተሰብ አባላት በሚቀርቡ ሌሎች አገልግሎቶች ላይ በመታደም ተሳትፎ አደርጋለሁ፤
   - የጊዜ ሰሌዳ በተያዘለት እና የተፈቀደ የልጄ ጉብኝት ላይ በንቃት እሳተፋለሁ፣ እንዲሁም
   - ለልጄ አገልግሎቶችና ምደባ በFAPT እና ኤጀንሲው የሚፈለጉ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችና ሰነዶች አቀርባለሁ።

4. ለህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋሙ የሚከተሉትን እሰጣለሁ:
   - ድንገተኛና ህክምናን ጨምሮ ለመደበኛ ህክምናና እንክብካቤ የሚሰጥ የጽሁፍ ፍቃድ። የቀዶ ህክምናን ወይም የአእምሮ ማደንዘዣ መድሀኒቶች ህክምናን ጨምሮ ለትኛውውም የታቀደ በልጄ ላይ ከፍተኛ ስጋት የሚያስከትል ህክምና ወይም አገልግሎቶች በልዩ መረጃ የተደገፈ ፍቃድ ማግኘትን ይጠይቃሉ።
   - ሁሉንም እኔን ማግኛ የድንገተኛ ጊዜ ስልክ ቁጥሮች።

5. እኔ/እኛ ለልጄ በሚሆኑ አገልግሎቶች ላይ ለመሳተፍ በአካባቢው ለመቆየት ተስማምቻለሁ/ተናል። እኔ/እኛ ከ2 ሳምንታት በላይ በአገልግሎቶች ውስጥ በንቃት መሳተፍ እንዳንችል የሚያደርግ ከባድ ሁኔታ ካለ፣ ሁኔታውን ለCPMT ወዲያውኑ ለማሳወቅ እኔ/እኛ ተስማምቻለሁ/ተናል። የእኔን/የእኛን መቅረት ሙሉ CPMT አስቀድሞ ማጽደቅ አለበት።

6. በወቅታዊ የመኖሪያ ቦታዬ ለሚገኘው CPMT የመኖሪያ ቦታዬን ከግዛቱ ውጭ ለመቀየር ስላለኝ ስለየትኛውም እቅድ ለማሳወቅ እስማማለሁ።

**መብቶች እና ኃላፊነቶች፡**
**በCPMT የተመደበ ኤጀንሲ**

ኤጀንሲው በሚከተሉት ይስማማል፥

- የጉዳይ አስተዳደር አገልግሎቶችን አዘጋጅቶ ለማቅረብ እና IFSPን ለመተግበር ከእኔ/እኛ እና ልጄ/ልጃችን ጋር አብሮ ለመስራት፣
- በተደነገጉት የCPMT የአካባቢ ፖሊሲዎችና ሥነ ሥርአቶች እና በተገቢ ህግ መሰረት ለእኔ/እኛ ጉዳይ ተኮር መረጃ ለመስጠት፣ እና
- በተደነገጉት የCPMT ፖሊሲዎችና ሥነ ሥርአቶች መሰረት የአጠቃቀም አስተዳደር/ቁጥጥር ለማቅረብ።

**የፊስካል ባለስልጣን/የክፍያ ድንጋጌዎች**

የአገልግሎቶች ክፍያዎች በCPMT በሚጸድቁት ፖሊሲዎችና ሥነ ሥርዓቶች መሰረት በሁሉም ወገኖች ተከፍለው በሰነድ የሚመዘገቡ ሲሆን የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ

- የወላጅ የጋራ ክፍያ፣
- የመድን ዋስትና ፖሊሲዎች፣
- የልጅ ድጋፍ (የህጻን ድጋፍ አስፈጻሚ ምድብ)፣
- የፌደራል እና/ወይም የግዛት የድጋፍ ምንጮች፣ እና
- የCSA ስምሪት የገንዘብ ድጋፎች

1. በCSA በሚሸፈን ገንዘብ የሚፈጸመው የአገልግሎት ወጪዎች ክፍያ የሚጸድቀው በCPMT በወጡት ፖሊሲዎች እና አሰራሮች መሰረት በተፈቀደው በIFSP ውስጥ ለተካተቱት እና አግበብነት ላላቸው የከተማ/የሀገሪቱ የግዢ እና የበጀት ፖሊሲዎች ተገዢ ለሆኑ አገልግሎቶች ብቻ ነው።

2. ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች ምደባው በተካሄደ በ30 ቀናት ውስጥ በIFSPው መሰረት የሚቀርቡትን አገልግሎቶች ክፍያ ለመክፈል እንዲያግዛቸው ለMedicaid፣ FAMIS፣ እና/ወይም ሌሎች የመንግስት ወይም የገንዘብ ድጋፎች እና የድጋፍ ምንጮች ለማመልከት ይስማማሉ።

3. ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች የMedicaid ብቁነት ማስታወቂያ ከደረሳቸው በኋላ በIACCT አሰራር (የገለልተኛ ጥናት ማረጋገጫ ሰጪና አስተባባሪ ቡድን) ላይ ለመሳተፍ ይስማማሉ። የIACCT አሰራር Medicaid ለምደባው በከፊል የገንዘብ ድጋፍ ስለማድረግ አለማድረጉ ይወስናል።

4. ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች እንደ ተግባራዊነቱ ምደባው በተካሄደ በ30 ቀናት ውስጥ በIFSPው መሰረት የሚቀርቡትን አገልግሎቶች ክፍያ ለመክፈል እንዲያግዛቸው ለMedicaid፣ FAMIS፣ እና/ወይም ሌሎች የመንግስት ወይም የገንዘብ ድጋፎች እና የድጋፍ ምንጮች የማያመለክቱ ከሆነ የአርሊንግተን ካውንቲ ወላጆች ለMedicaid እስከሚያመለክቱበት ጊዜ ድረስ ለዚህ ምደባ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈል አይፈቅድም። ከምደባው በኋላ ወላጆች የሚሰጠውን ህክምና እና/ወይም ትምህርት ወጪዎች የመክፈል የገንዘብ ኃላፊነት አለባቸው።

5. ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች በCPMT ፖሊሲዎች እና ሥነ ሥርዓቶች መሰረት የሚወሰነውን የወላጅ የጋራ ክፍያ ለመክፈል ይስማሙ።

6. ከዚህ በተጨማሪም ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች አልባሳትን፣ የሽንት ቤት ቁሳቁሶችን፣ ራስን መንከባከቢያ ቁሳቁሶችን፣ የኪስ ወጪ አበሎችን እና ተጨማሪ እዚህ ላይ የተዘረዘሩ ቁሳቁሶችን ጨምሮ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን ከልጆቻቸው እንክብካቤ ጋር በተያያዘ የተወሰኑ መደበኛኛ የተለመዱ የወላጅ ኃላፊነቶች የሆኑ የገንዘብ ኃላፊነቶች ይኖሩባቸዋል፥

---

7. ተዋዋይ ወገኖች የቨርጂንያ የሕጻናት አገልግሎቶች ጽ/ቤት (Virginia Office of Children's Services) ("OCS") የዚህ ስምምነት አንድ ተዋዋይ ወገን መሆኑን እና CPMT በዚህ ስምምነት ላይ ያኖረው ፊርማ በዚህ ውስጥ ስሙ የተጠቀሰው ወላጅ(ጆች) ወይም ህጋዊ አአሳዳጊ(ዎች) ስምምነት ላይ የተደረሰበትን የገንዘብ መጠን በወቅቱ ሳይከፍል ቢቀር ወይም ለመከፈል ፈቃደኛ ባይሆን በዚህ ወላጅ(ጆች) ወይም ህጋዊ አሳዳጊ(ዎች) ላይ የክፍያ ጥያቄ የማቅረብ ስልጣን ለOCS ለመስጠት ዓላማ ሲባል በOCS ስም እንደተፈረመ ተደርጎ የሚቆጠር መሆኑን ተስማምተዋል። ይህ በOCS የሚቀርብ የክፍያ ጥያቄ የCPMT ጥያቄ ሲቀርብ ብቻ እና የገንዘብ ስብሰባው ተግባር ወደ ማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ የህጻናት ድጋፍ አስፈጻሚ ምድብ መመራት በማይችልበት ጊዜ በህግ መምሪያ የእዳ ስብሰባ ምድብ በኩል ብቻ ይቀርባል።

8. ወላጁ(ጆቹ)/ሕጋዊ አሳዳጊው(ዎቹ) በዚህ CPMT ከተወከለው ከተማ/ሐገር ወጥተው ከሄዱ በአዲሱ የቨርጂንያ አካባቢ ወይም በሌላ ግዛት ሕጋዊ የስልጣን ክልል ውስጥ ያለው CPMT ይህን ስምምነት አክብሮ ለመፈጸሙ ምንም አይነት ዋስትና አለመኖሩን እና ይህ የልጃቸው ምደባ ሊቋረጥ እንደሚችል ያውቃሉ። ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች በተጨማሪም አሁን ለሚገኙበት አካባቢ CPMT ከግዛቱ ውጭ የመኖሪያ አድራሻቸውን ለመቀየር ስላላቸው ስለየትኛውም እቅድ ለማሳወቅ ይስማማሉ።

ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች በተጨማሪም የመኖሪያ ቦታቸውን የሚቀይሩ ከሆነ የሚከተሉትን ይገነዘባሉ፥

- የመኖሪያ ቦታቸውን የሚቀይሩት ቨርጂንያ ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ ከሆነ አዲሱ የመኖሪያ ቦታ በቦታው የCPMT ፖሊሲዎች መሰረት የትኞቹ ተገቢ አገልግሎቶች እና ስምምነቶች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ የሚወስንበት እስከ **30** የካላንደር ቀናት ይኖረዋል። **30** የካላንደር ቀናቱ ለአዲሱ CPMT የአድራሻ ለውጡን የተመለከተ የጽሁፍ ማስታወቂያ ከሚደርስበት ቀን ይጀምራሉ። ይህ የወላጅ ስምምነት የአዲሱ የመኖሪያ ቦታ CPMT አገልግሎቶቹን ተግባራዊ ሲያደርግ ወይም **30** የካላንደር ቀናቱ ሲያበቁ፣ ከሁለቱ የትኛውም የቀደመው ሲከሰት ይቋጣል።
- የመኖሪያ ቦታቸውን የሚቀይሩት ከቨርጂንያ ውጭ ወደሚገኝ የመኖሪያ ቦታ ከሆነ ይህ በህግ የማይጠየቅ ስምምነት ወዲያውኑ ይቋረጣል፤ ማለትም CPMT ለምደባው የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉን የመቀጠል ግዴታ የለበትም እንዲሁም የህጻኑን ምደባና እንክብካቤ ኃላፊነት ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች ይወስዳሉ።

## ስምምነቱ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

ይህ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ስምምነት ነው። የልጁ ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ እንደመሆኔ ይህን ስምምነት በየትኛውም ጊዜ መሻር እንደምችል እገነዘባለሁ። ከዚህ ስምምነት ማብቂያ ጊዜ በፊት ልጁ ወደ እኔ እንዲመለስልኝ የምጠይቅ ከሆነ ልጁ ወደ እኔ ይመለሳል ብዬ ካቀድኩበት ቀን ከ **30** ቀናት በፊት የጽሁፍ ማስታወቂያ እሰጣለሁ።

ኤጀንሲው ስምምነቱ የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች እና ለምክንያቶቹ ደጋፊ የሆኑ ሰነዶችን ጨምሮ ለእኔ የ **30** ቀናት የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ይህን ስምምነት ሊያቋርጥ እንደሚችል እረዳለሁ። ምክንያቶቹ፡ የኤጀንሲው የአጠቃቀም አስተዳደር ምርመራ ወይም ሌላ ምክንያት ላይ ተመስርቶ ምደባው የህጻኑን ጥቅም አያስከብርም፣ እጅግ ተገቢ አይደለም ወይም የህጻኑን ፍላጎቶች ለማሟት ገዳቢ መቼት ነው ብሎ መወሰንን፤ ወይም የህጻኑ በምደባው በበቂ ሁኔታ መሻሻል አለማምጣትን፣ ወይም የእኔ የዚህን ስምምነት ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን አለማሟላትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።

**የይግባኝ አሰራር**

በኤጀንሲው ይህን ስምምነት የማቋረጥ ውሳኔ የማልስማማ ከሆነ የአካባቢውን CPMT የይግባኝ ፖሊሲዎችና ሥነ ሥርዓቶች ተከትዬ የጽሁፍ ጥያቄ በማስገባት እና ከዚያ በኋላ በስራ ላይ ባለ ፖሊሲ ወይም ህግ ስር በተቀመጡ በየትኛውም ተፈጻሚ አሰራሮች አማካኝነት በውሳኔው ላይ ይግባኝ የማለት መብት እንዳለኝ እረዳለሁ። ይህን ስምምነት በመፈረም የአካባቢውን የCPMT የይግባኝ ፖሊሲዎችና ሥነ ሥርዓቶች መቀበሌን አረጋግጣለሁ።

**ፊርማዎች**

የዚህ ስምምነት ግልባጭ ለሁሉም ፈራሚ ወገኖች የሚሰጣቸው ሲሆን ዋናው በ2100 Washington Blvd. Arlington VA, በሚገኘው የልጁ ፋይል ውስጥ ይቀመጣል። ከዚህ በታች በመፈረም እያንዳንዱ ወገኖች እዚህ ላይ በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት የዚህ ስምምነት አካል ይሆናሉ።

| | |
|---|---|
| **ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ** | **ቀን** |
| **ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ** | **ቀን** |
| **በCPMT**<br>**የተወከለው ኤጀንሲ ተወካይ** | **ቀን** |